ምስጢረ ቀንዲል

ጥያቄ፣- ምስጢረ ቀንዲል ማለት ምን ማለት ነዉ?

ምስጢረ ቀንዲል ማለት ምስጢረ ቅብዐ ፈውስ ማለት ነው።

ምስጢረ ቀንዲል ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ነው። ምስጢረ ቀንዲል የተጀመረው በጌታ ችን ዘመን በሐዋርያት ነው። ይኽውም ቅዱሳን ሐዋርያት በጌታችን ትእዛዝ ልዩ ልዩ ድውዮችን (በሽተ ኞችን) ቅብዐ ቅዱስ እየቀቡ ይፈውሱ ነበር (ማር. 6፣12-13)።

የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረዉ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ምስጢረ ቀንዲልን አስመልክቶ ስምእ መናን ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፤ «ከእናንተ መከራ የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለዉ ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር (ጌታን ያመስግን)። ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር እርሱ የቤተክርስቲያን ን ቀሳዉስት ወደእርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተዉ ይጸልዩለት። የእምነት ጸሎት ድውዩን (በሽተኛዉን) ያድናል፤ ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆን ይሰረይለታል» (ያዕ. 5፣ 13-15)።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምስጢረ ቅብዐ ፈውስ የሚፈጸምላቸው ሕመማን፤ በኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት የሚከ ተሉ መሆን አለባቸው።

ምእመናን ልዩ ልዩ በሽታ ሲያድርባቸው ወደ ቤተክርስቲያናቸው ማለት ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያናቸ ው እየሄዱ ወይም መልእክተኞች እየላኩ ቀሳዉስቱ በጸሎት ምስጢረ ፈውስ (ምስጢረ ቀንዲል) ይፈ ጽሙላቸው ዘንድ ይገባል።

ጥያቄ፣- ምስጢረ ቀንዲል መፈጸም የሚችል ማን ነዉ?

ምስጢረ ቀንዲልን መፈጸም የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ቀሳውስት ናቸው፤ ማለት በአንብሮተ እ ድ የተሾሙ ቀሳውስት ይህንን የፈውስ ምስጢር በሕመማን ላይ መፈጸም ይችላሉ። ሥልጣነ ቅስና የሌ ለው ሰው ግን ምስጢረ ቀንዲልን መፈጸም አይችልም።

ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት 1991 አቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ።